# የኔ ብዕር ሴረኞችን እንቅልፍ መንሳቱና መርዝ መሆኑ እርግጥ ነው!

(ፍቅሩ አየለ በላይ፣ ከሸበል በረንታ)

ይህ ጽሁፍ ዛሬ ነሀሴ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በወጣው በሰንደቅ ጋዜጣ 6 ኛ ዓመት ቁጥር 310 ላይ ታትሞ ለንባብ የቀረበ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ:: ይሁን እንጂ፣ በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በ Ethiofact ድረ ገጽ ላይ ተመሳሳይ የሃሳብ ልውውጥ እየተደረገ ስለሆነ ለአንባብያን ግንዛቤ ይረዳል በሚል እምነት እነሆ እዚህም ላይ እንዲታተም ተደርጓል:: ወደ ርእሰ ጉዳዩ እናምራ!

ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም በታተመው ሰንደቅ ጋዜጣ 6 ኛ ዓመት ቁጥር 308 ላይ "ይደረስ ለዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳ" በሚል ርእስ ላቀረብኩት መጣጥፍ፣ ከዶ/ር ነጋሦ የጥብቅና ውክልና መያዛቸውን በቅጡ ያልገለጹልን አያልቅበት ፍቅሩ የተባሉ ጸሐፊ "ጥላቻ ያረገዘ ብእር መርዝ ነው የሚተፋው" በሚል ርእስ ያቀረቡትን ጽሁፍ ከዚሁ ጋዜጣ ቁጥር 309 የነሀሴ 4 ቀን 2003 ዓ.ም እትም ላይ አነበብኩና አፎቱ ውስጥ የተከተተ ብሬን ዳግም ለመምዘዝ ተገደድኩ።

ጸሐፊው አቶ አያልቅበት በጽሁፋቸው መግቢያ ላይ "ምክር መሰል" ትንታኔ እንደ መነሻ አቅርበዋል። ክፋቱ በሌሎች ላይ ያለን ጉድፍ ለማመላከት ሲፍገመገሙ የራሳቸው ግንድ የሚያህል "ጉድ" ሊታያቸው ባለመቻሉ፤ በሌሎች ላይ "አለ" የሚሉት የጥላቻ መርዝ በእርሳቸው የብር ጫፍ በከፋ መልኩ ሲንጠባጠብ ይስተዋላል። እናም አንድ በአንድ ላሳያቸው ወደድኩ።

- **"የዘር ጥላቻና የሃይማኖት መርዝ የሚረጭ በጥላቻ የተሞላ..." የሚለውን በተመለከተ፣**

የእኔን ስህተት መፈለግን የጽሁፋቸው ዋነኛ ዓላማና ግብ አድርገው የተነሱት አቶ አያልቅበት ከሁሉ አስቀድመው ያነሱት ነጥብ የእኔ ጽሁፍ "የዘር ጥላቻና የሃይማኖት ልዩነት መርዝ የሚረጭ" መሆኑን ለማሳየት ነው። እርሳቸው ራሳቸው የጥላቻ ስንቅ ቋጥረው ጉዟቸውን የሚጀምሩትም እዚሁ ላይ ነው። አንድ ሰው ሃሳቡን ስለገለጸ "ጥላቻ እየነዛህ ነውና ዝም በል" ማለት ትልቁ ስህተት ነው። እንዲህ ያለው ተራ ማሸማቀቅ የተነቃበት ይትበሃል ስለሆነ በዚሁ አልፈዋለሁ። የሌሎችን አፍንጫ ሳልነካ፣ ሃሳቤን ያለ ምንም ገደብ መግለጼን እቅጥላለሁ።

አንባብያን እንደምታስታውሱት ባለፈው ጽሁፌ በቅንጅት ውስጥ ከመጋረጃው በስተጀርባ ሲውጠነጠኑ የነበሩ አራት ዋና ዋና ሴራዎች ተንትኜ አቅርቤ ነበር። ከያንዳንዱ ሴራ በስተጀርባ እነማን እንደነበሩ ለማሳየትም ሞክሬአለሁ። አቶ አያልቅበት የዛሬ ሳምንት ባቀረቡት ጽሁፍ ማስጃ አቅርበው አንዱንም ሴራ ለማስተባበል አልቻሉም። እንዲያውም እነዚያ እኔ የጠቀስኳቸው ሴራዎች እንደነበሩ አያልቅበት በጽሁፋቸው ላይ በማመላከት የኔን ሃሳብ ያጠናከሩበት ሁኔታ ነው የታየው። (ይህንን ወደኋላ ላይ እመለስበታለሁ)

አቶ አያልቅበት የእነዚያን ሴራዎች አለመኖር ማሳየት ሲያቅታቸው እኔን ለማሸማቀቅ በደፈናው "የዘር ጥላቻና የሃይማኖት ልዩነት መርዝ ትረጫለህ" የሚል ክስ ያቀርቡብኛል:: እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ላቅርብልዎ አቶ አያልቅበት፣ ሰዎች ዘርን መሰረት ያደረገ ቡድን መመስረታቸውና የአንዱን ሃይማኖት ተከታዮች እያገለሉ ሌላውን እንዲሰባሰብ ማድረጋቸው ነው "መርዝ" የሚሆነው ወይስ እንዲህ ዓይነት "መርዝ" እየተረጨ ነበር ብሎ መጻፍ? በበኩሌ በወቅቱ የተውጠነጠነውንና (ከሞላ ጎደል እርስዎም ያልካዱትን) ጠንቀኛ ሴራ እንዲታወቅ ማድረጌ ብዕሬን መርዘኛ ሊያሰኘው አይችልም ባይ ነኝ። የኔ ብዕር ሀቅን መጋፈጥ ለሚፈሩ፣ እውነትን ለማየትና ለመስማት ለማይሹ ሴረኞች መርዝ መሆኑ ግን እርግጥ ነው!

- **አሁንም ቅንጅት "ተቋም" አልነበረም፣**

ባለፈው ጽሁፌ "ቅንጅት ተቋም አልነበረም። በዚህ ረገድ ወ/ሪት ብርቱካን 'ቅንጅት መንፈስ ነው' ማለቷ ትክክል ነበር" በማለት ያቀረብኩትን ሃሳብ ለመተቸት የተነሱት አቶ አያልቅበት እንዲህ ይላሉ፣ "...'ቅንጅት ተቋም አልነበረም' ብለው ሦስት መስመር ሳይሄዱ ደግሞ 'ምርጫውን በጋራ ለመሳተፍ ከተስማሙ አራት ድርጅቶች የተወከሉ 16 ሰዎች ብቻ ነበሩ እንደ 'ስትሪንግ' ኮሚቴ ሆነው ሲሰሩ የነበሩት' ብለዋል። ማስተዋል አልቻሉ ሆኖ ነው እንጂ ይህ አባባላቸው ብቻ ቅንጅትን ተቋም ያሰኘዋል" ይላሉ ጸሀፊው።

ወይ አያልቅበት! ማስተዋልስ ያልቻሉት እርስዎ ነዎት ወዳጄ! የ 16 ሰዎች ስብስብ የሆነ ኮሚቴ በየትኛው መመዘኛ ነው 'ተቋም' የሚሰኘው? ምርጫን በጋራ ለመወዳደር ተስማምተናል ብሎ መፈራረምና ያንን ፊርማ በምርጫ ቦርድ እንዲመዘገብ ማድረግስ ቅንጅትን "ተቋም" ያሰኘዋል ነው የሚሉት? አንድም የግለሰብ አባል ያልነበረውን አካል "ተቋም ነው፣ ሀገር ሊመራ የሚችል ፓርቲ ነው" ማለት በዓለም የድንቅ ስራዎች መዝገብ ላይ ለመመዝገብ ታስቦ ካልሆነ በስተቀር ትርጉም ያለው አይመስለኝም:: ያውም ሀገር ሊመራ የሚችል ተቋም! በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያኔ ያላገጡት አይበቃም አያልቅበት?! መከሰስንም ለቅንጅት "ተቋም" መሆን በማረጋገጫነት ጠቅሰዋል አያልቅበት።

ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ “ተቋም” የሚለው ቃል (ጽንሰ ሐሳብ) ምን ትርጉም እንዳለው ሰነዶችን ፈትሾ፣ መጽሐፍትን አገላብጦ አንድ ቁም ነገር ማቅረብ ለጋራ ግንዛቤ ስለሚረዳ ወዳጄ አያልቅበት ጊዜ ካለዎት በዚህ ጉዳይ ላይ ቢተጉ መልካም ነው። እኔ ባለኝ መረጃ ተቋም ማለት፣ “መዋቅራዊ ይዘት ያለውና በተወሰነ የሰው ኃይል የተደራጀ ክለብ፣ ማህበር፣ የንግድ ድርጅት እና በአዋጅ ወይም በህግ የተሰጠ ኃላፊነት ያለው አስተዳደራዊ ስርዓትን ያመለክታል” ይላል።

ከዚህ ትርጉም ስንነሳ ቅንጅት ግለሰብ አባል አልነበረውም። በሰው ኃይልም አልተደራጀም። መዋቅርም አልነበረውም። እናም “ተቋም” አልነበረም። “ተቋም አልነበረም” ማለት ግን ሕጋዊ እውቅና አልነበረው ማለት አለመሆኑን ልብ ማለት ይገባል። “አመራሮቹ” የተከሰሱትም “ተቋም” ስለሆነ ሳይሆን ህጋዊ እውቅና ስለነበረው ነው። የእኔ አቋም ይኸ ነው። ከፈለጉ እርስዎ “ቅንጅት ተቋም ነበር” ማለት መብትዎ ነው። ግን ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያኔ የዋሸነው አይበቃም አያልቅበት?

- **ቅንጅት ከምርጫ በኋላ ስለመፍረሱ፣**

አያልቅበት ካለው ጽሁፌ ላይ፣ “ቅንጅት ከምርጫ በኋላ እንደሚፈርስም ፈርመውና ማህተም አትመው ስምምነቱን አጽድቀው እንደነበርም የሚታወስ ነው” የምትለዋን ሃሳብ ቀንጭበው ከጠቀሱ በኋላ፣ “አቶ ፍቅሩ ይህን ሲሉ ከፍተኛ አመራር ነበርኩ ማለታቸውን የዘነጉ ይመስላል። ምክንያቱም የገለጹት ስምምነት ተደርጎ ከሆነ ራሳቸውንም መግለጽ ነበረባቸውና ነው” የሚል አስተያየት አስከትለዋል። በዚህም አያቆሙ። ቀጥለው ደግሞ፣ “የጥላቻ ክፋቱና የሚያስከትለው አደጋ ከባድነት የሌሎችን ብቻ ሳይሆን የራስንም ስራ ለማየት አለማስቻሉ ነው” በማለት ችኩልና መሰረት የሌለው ትችት ይሰነዝራሉ።

አቶ አያልቅበት የምርጫውን ሂደት ያስፈጸመው ቅንጅት እና ከመስከረም 14 ቀን 1998 በኋላ በውህደት ስምምነት የተዋቀረው ቅንጅት እኮ የተለያዩ ናቸው። የምርጫውን ሂደት ያስፈጸመው ከአራቱ ፓርቲዎች አራት አራት ሰዎች የተወከሉበት የ 16 ሰዎች ስትሪንግ ኮሚቴ ነው። በዚህ ውስጥ እኔ አልነበርኩም። በሌለሁበት የተወሰነ ውሳኔ እኔን ሊመለከተኝ አይችልም። መስከረም 14 ቀን 1998 አራቱ ፓርቲዎች በግሎባል ሆቴል ባደረጉት “የውህደት ስምምነት” መሰረት 60 የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ተሰይመው ነበር። በዚያ ውስጥ ነበርኩ። የሁለቱን ልዩነት እያወቁ፣ እኔ በየትኛው አካል ውስጥ አባል እንደነበርኩም ልቡናዎ እያወቀ፣ በክፋት ስሜት ተነሳስተው “ራስህን ገለልተኛ ያደረግከው በውስጥህ ጥላቻ ስላለ ነው” ይሉኛል? ነገር ነገሩ ‘ሌባ እናት ልጇን አታምንም’ ነውና በታላቅ ትዝብት አልፈዋለሁ።

አቶ አያልቅበት በዚሁ ጽሁፋቸው እንዲህም ብለውኛል። “ከፍተኛ አመራር ነበሩ። በቅንጅት ተወዳድረው ለአምስት ዓመታት ፓርላማም ቆይተዋል” ይሉኛል። አቶ አያልቅበት ባለፈው ጽሁፌ በየትኛው ቦታ ላይ ነው በምርጫ ተወዳድሬ ፓርላማ ገብቻለሁ ያልኩት? ከየት አመጡት? ነቢይነት ነው፣ ጥንቆላ ነው ወይስ በሳይሆን አይቀርም ጥርጣሬ? ውድ አንባብያን ታዲያ ከዚህ በላይ የጥላቻ መርዝ አለ? አንባብያን እንደምታስታውሱት ያለፈው ጽሁፌን ያቀረብኩት በብዕር ስም ነው። ማንነቴን የሚያውቀው የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል ብቻ ነው። ዝግጅት ክፍሉ የኔን ማንነት ለአቶ አያልቅበት እንደማይገልጽም ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለኝም። ምናልባት አቶ አያልቅበት የሌላ ጋዜጣ አዘጋጅ ከነበሩና በዚያ አጋጣሚ ማንነቴን አውቀው ከሆነም በስራ አጋጣሚ ያገኙትን ሚስጥር ከቅን ልቦና ውጪ በመጠቀምዎ በሕግ የሚያስጠይቅዎ መሆኑን ከኔ በላይ እንደሚያውቁ እረዳለሁ።

ቅንጅት ሀገር መምራት የማይችል መሆኑን በተመለከተ ያኔም ስናገር ነበር። (አያልቅበት ካወቁኝ በወቅቱ የወጡ ጋዜጦችን መመልከት ይችላሉ) አሁንም እየተናገርኩ ነው። እንዳስፈላጊነቱ ወደፊትም እናገራለሁ። ግን ማን ሰምቶ! ያኔ አያልቅበትና መሰሎችዎ አይታችሁት የማታውቁትን “Protest Vote” ስታዩ “አሁን ገና ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን እንደምችል አረጋገጥኩ” እያላችሁ በየአደባባዩ ትታበዩ ስለነበር ስለቅንጅት ቅንጣት ታህል አሉታዊ ሃሳብ መስማት ስለማትፈልጉ የምንናገረውን ልትሰሙን አልፈለጋችሁም። እስቲ አሁንም እግረ መንገዴን አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎ። ያኔ ቅንጅት አማራን ወይም ኦሮሚያን ወይም ደቡብ ክልልን አሸንፈሃልና ተረከብ ቢባል ኖሮ ፕሬዝዳንት ሆኖ ክልሉን መምራት የሚችል ሰው ነበር? ሌላው ቀርቶ እንደ ፓርቲ የመንፈስ ዝግጅቱስ ነበር? ለክልል ምክር ቤት በእጩነት የቀረቡት ሰዎች ዝርዝር ከነ ትምህርት ደረጃቸው አሁንም በእጄ ይገኛል። አንድም በዲግሪ ወይም በዲፕሎማ የተመረቀ ሰው እጩ አልነበረም። ከሁሉም ፓርቲዎች ጥሩ የትምህርት ዝግጅት የነበራቸው አባላት ለተወካዮች ምክር ቤት ነበር የቀረቡት። የነሱም ብቃት ባለፉት አምስት ዓመታት በተግባር ታይቷል። ከፊሉ በማጭበርበርና በስርቆት፣ ሌላው በአስገድዶ መድፈር ሲካሰሱ እንደነበር አይተናል፣ ሰምተናል። እነዚህ ናቸው ከኢህአዴግ የተሻለ አመራር ሊሰጡ የሚችሉት?

- **ከቅንጅት የውህደት ሂደት በስተጀርባ የተሸረበውን ሴራ በተመለከተ፣**

አንባብያንን ለማስታወስ ያህል ባለፈው ጽሁፌ በቅንጅት ውስጥ ከመጋረጃው በስተጀርባ ይውጠነጠኑ የነበሩ አራት ዋና ዋና ሴራዎችን በመጥቀስ፣ ቅንጅትን ያፈረሰው እንዲህ ያለው ሴራ፣ ተንኮልና ሸር ነው ብዬ ነበር። አቶ አያልቅበት ለኔ መልስ ብለው ባቀረቡት ጽሁፋቸው እነዚህን ሴራ ብየ የጠቀስኳቸውን ፍሬ ሃሳቦች የሚያጠናክር እንጂ የሚያፈርስ ሃሳብ አላቀረቡም። ይህንንም እንደሚከተለው አብራራለሁ።

(1) በኔ በኩል ሴራ ብየ ያቀረብኩት አንዱ ሃሳብ “ቅንጅት በውህደት ሲመሰረት ከአራቱ ፓርቲዎች ለአመራርነት እነማን መምጣት እንዳለባቸውና እነማን መወገድ እንዳለባቸው የተጠነሰሰ ሴራ ነበር” የሚል ሲሆን፣ አያልቅበት ይህንን በተመለከተ “የቅንጅት አመራር ከአራቱ ፓርቲዎች በኮታ የተዋቀረ [ነው] … ታዲያ ሀቁ ይህ ከሆነ ቅንጅቱ የተጠናከረ ተግባብቶ የሚሰራ ለህዝብ የገባውን ቃል ከግብ ለማድረስ የሚያስችለው አመራር እንዲኖረው እነ እገሌን ፓርቲያችሁ ቢልክ የሚል የማግባባት ስራ ተሰርቶ ከሆነ ይህ ዴሞክራሲያዊ አግባብ ነው” ይላሉ።

አቶ አያልቅበት ለዚህ አባባልዎ ምስጋና ይገባዎታል፡፡ ሀቁን ተናግሮ እመሸበት ማደር መልካም ነው። ያቀረብኩት የሴራ ትንተና ትክክል መሆኑን ምስክርነትዎን ሰጥተዋል። ግን ግን ማን ነው ማንን እነ እከሌን ላክ እነ እከሌን አትላክ የሚል ትእዛዝ የመሰጠው? በምን መስፈርት? ከበስተጀርባ መሽጎ ተንኮል የሚተበትበው ሴረኛ ቡድን ይህንን እንዲያደርግ ማን ፈቀደለት? ደግሞስ ለቅንጅት የበለጠ ተቆርቋሪ የሆነው በምን ምክንያት ነው? እንዲህ ያለው የተንኮል መንገድ “ዴሞክራሲያዊ” የሚሰኘው በየትኛው መስፈርት ነው አቶ አያልቅበት? ለቅንጅቱ አመራር ጠንካራ ሰዎችን ግልጽ በሆነ መንገድ እንምረጥ ማለት አንድ ነገር ነው። እነ እከሌ ይምጡ እነ እከሌ እንዳይመጡ ብሎ ውስጥ ለውስጥ መንሾካሾክ ነው “ዴሞክራሲያዊ” አሰራር? በሌላ በኩል ሴራው የተዶለተባቸው ሰዎች ይህንን ሴራ ለመበጣጠስና ለማምከን ተግተው ቢሰሩስ ስህተት ነው?

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አቶ አያልቅበት ሌላ አስቂኝና ከላይ ከተናገሩት ጋር የሚጋጭም ሃሳብ ጽፈዋል። “አመራሩ የተዋቀረው በኮታ ከሆነ ምርጫው የሚካሄደው በየፓርቲዎቹ ስለሆነ ቅንጅት ውስጥ የተባለው ድርጊት የሚፈጸምበት አግባብ የለም” ይላሉ። አቶ አያልቅበት ኮታው የአራቱ ፓርቲዎች የስምምነት ውጤት ስለሆነ ችግር የለውም። ችግሩ ያለው በዚያ ኮታ መሰረት ወደ ቅንጅት አመራርነት የሚመጡት ሰዎች እነ እከሌ ይሁኑ፣ እነ እከሌ እንዳይመጡ የሚለውና ማንነቱ ካልታወቀ ሴረኛ ቡድን የሚመጣው ሕቡዕ መመሪያ ላይ ነው። ይህ ደግሞ እንደነበር እርስዎም አምነዋል። ያመኑበትን ጉዳይ ከላይ ገልጸው ዝቅ ብለው የሚዘነጉት ከሆነ ያው የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች “የዝንጉነት” (Short lived Memory) ችግር አድርገን ከመውሰድ ውጪ ሌላ ምን ይባላል!

ጸሐፊው በቅንጅት ውስጥ የነበረውን የስልጣን ሽኩቻም ኮንነው ጽፈዋል። አቶ አያልቅበት ሰዎች ፖለቲካ ውስጥ የሚገቡት እኮ (አመንበትም አላመንበት) ለስልጣን ነው። ለስልጣን መሻኮት ደግሞ እንኳን እንደ እኛ ባለ የሰለጠነ ፖለቲካ በማናራምደው ፖለቲከኞች በሰለጠኑትም ሀገሮች ያለ ነው። እርስዎም ቢሆኑ ፖለቲካ ውስጥ የገቡት መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ እንዳልሆነ ልቦናዎ ያውቀዋል። ሂደቱ በዴሞክራሲያዊ መንገድ እስከሆነ ድረስ መሻኮቱ ሀጢያት አደለም። ሀጢያት የሚሆነው ሴረኛና አፋኝ ቡድን አደራጅቶ (Gang-up አድርጎ) አንዱን ለመጣልና አንዱን ለማንሳት የተንቀሳቀሱ እንደሆነ ነው። በቅንጅትም ውስጥ የታየው ይኸው ሴረኛነት ነበር።

(2) ሴራ ብዬ ያቀረብኩት ሁለተኛው ነጥብ፣ “ምርጫን ተገን በማድረግ ስልጣንን ‘ከትግሬዎች’ የመቀማት ሴራ” የሚል ነው፡፡ አያልቅበት ይህንንም አላስተባበሉም፡፡ ይልቁንም ሴራው በሚያስከትለው ውጤት ላይ አተኩረው “አንተንም ያስጠይቅሃልና እንዲህ ያለውን ነገር መነካካትህ ተገቢ አደለም፡፡ በሳት መጫወት ነው” የሚል መንፈስ ያለው ሃሳብ ይዘበዝባሉ። አዛኝ ቅቤ አንጓች ባይሆኑ ምናለ አቶ አያልቅበት!? አህያውን ትተው ዳውላውን ፍለጋ መባዘኑ የትም አያደርስም። ካጠፋሁና መጠየቅ ካለብኝ መጠየቅ አለብኝ እንጂ እናቴ ሆድ ተመልሼ ለመግባት መወራጨት የትም አያደርሰኝም። ስለዚህ በዚህም ረገድ የነበረውን ሀቅ ማፍረጥረጥ እንጂ ተጠያቂ ያደርገኛል በሚል መንፈስ ሽሽት ተገቢ አደለም። እስቲ አንድ ነገር በጥያቄ መልክ ላቅርብልዎ። አቶ አያልቅበት ያኔ ሚያዚያ 30 ቀን 1997 አቶ በድሩ አደም “ወደ መጡበት እንመልሳቸዋለን” ያሉት ከዚህ ጋር የሚያያዝ አይመስልዎትም? አቶ በድሩ ደግሞ በዚያ ወቅት ከእነማን ጋር እንደሚውሉና እንደሚያመሹ ይታወቃል። እና አቶ በድሩ ዝም ብለው በዚያች ቅጽበት የመጣላቸውን ሃሳብ ነው የተናገሩት ወይስ ከበስተጀርባ ሲከካና ሲቦካ የነበረውን? መልሱን ለእርስዎ እተዋለሁ።

ለነገሩ እርስዎም ቢሆኑ ሀቁ ሲተናነቅዎት አላስችልዎት አለና “...ከትግሬ ስልጣን መንጠቅ የሚባለው ነገር መጀመሪያ ሊመጣ የሚችለው መንግስቱ እንደዚያ ሲሆን ነው...” ካሉ በኋላ ብዙም ሳይርቁ፣ “አንዳንድ ግለሰቦች እንደዚያ ሊያስቡ ይችሉ ይሆናል... በፓርቲ መሪነት ላይ የተቀመጡ ግለሰቦች እንደዚህ ቢያስቡ እንኳ ፓርቲው...” ሊወቀስ አይገባውም በማለት ተንፍሰዋል። እንዲህ ያለው ወለም ዘለም ‘ሀቁን ብናገር ራሴን መወንጀል ይሆናል’ የሚል ግንዛቤ ከመፍጠር ውጪ ሀቁን ሙሉ ለሙሉ የሚክድ ባለመሆኑ በኔ በኩል “ነበር” ብየ የጠቀስኩትን ሴራ ውድቅ የሚያደርግ አይመስለኝም።

(3) አሁን ደግሞ አቶ አያልቅበት 3 ኛውን ሴራ በተመለከተ የሰጡትን አስተያየት እንመልከት። እኔ እንዲህ ነበር ያልኩት፣ “የአንድ እምነት ተከታዮችን ወደ አመራርነት የማምጣትና በተለይም ሙስሊሞችን ከአመራርነት የማግለል ሴራ” ይህንንም ሃሳብ ቢሆን አያልቅበት እውነቱን አረጋገጡ እንጂ ‘ሀሰት ነው’ ብለው አላስተባበሉም። ሃሳባቸው እንዲህ ይነበባል፣ “የመኢአድ አባላት ጠንቅቀው እንደሚያውቁት አቶ መሐመድም እንደሚመሰክሩት እርሳቸውን ከቅንጅት ምክር ቤት አባልነት ለማስቀረት ትግል የነበረው እዚያው ፓርቲያቸው ውስጥ ነው...” ይሉና አቶ አብዱራህማንን በተመለከተ ደግሞ “... በኢዴፓ ምክር ቤት አባላት እንጂ... ቅንጅት በዚህ ረገድ ምንም ድርሻ አልነበረውም” ይላሉ። አቶ በድሩን በተመለከተ ደግሞ “እሱ እንዲቀር የተደረገው ሚያዚያ 30 ባደረገው ዘረኛ ንግግር ነው” ይላሉ ጸሐፊው። የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መሰባሰብን በተመለከተ፣ “ለመሆኑ የተጠቀሱት ሰዎች ሁሉ የተባለው እምነት ተከታይ ስለመሆናቸው ምን ማረጋገጫ አላቸው? ቢሆኑስ ወንጀሉ ምንድነው?” ይላሉ አቶ አያልቅበት።

ከላይ የጠቀስኳቸው የአቶ አያልቅበት አባባሎች አንዳቸውም የኔን የሴራ ትንተና ፉርሽ የሚያደርጉ አደሉም። አቶ አብዱታህማንንና አቶ መሐመድ አሊን በተመለከተ ሴራው በፓርቲያቸው ውስጥ እንደነበር አቶ አያልቅበት አምነው 'ነገሩ ቅንጅትን ይመለከተውም' ነው ያሉት። ቅንጅትን በመሰረቱት አራቱ ፓርቲዎች ውስጥ ያለውን ሴራ እንዲቀሰቀስ ያደረገው እኮ "ወደ ቅንጅት አመራርነት እነማን ይሂዱ" የሚለውን በመመለሱ ሂደት የተከሰተ ነው። እናም ይሄ ቅንጅትን ከደሙ ንፁህ ሊያደርገው የሚችልበት አግባብ አይታየኝም፡፡ ደግሞም ቅንጅት የግለሰብ አባል ስላልነበረው ሽኩቻው በየፓርቲዎቹ ቢካሄድም፣ ሴራው ተቀምሞ የሚረጨው ቅንጅት ውስጥ ነበር።

አቶ በድሩ አደም የቅንጅት አመራር እንዳይሆኑ የተደረጉት ሙስሊም በመሆናቸው ስለመሆኑ በበኩሌ ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ቅንጅት ውስጥ ዘረኛና ነውረና ንግግር የተናገሩት እኮ እርሳቸው ብቻ አልነበሩም፡፡ የአንድን ክልል ህዝብ "ከፋብሪካ የወጣ ሳሙና" ያሉ ሰዎች አልነበሩም? በዚህ ረገድ ከኢ/ር ኃይሉ ሻውል የባሰ አፍ እላፊ የሚናገር ሰውስ አለ? ቅንጅትን ዘረኛ ንግግር ቢያሳስበው ኖሮ እነዚህ ሰዎች ወደ አመራርነት መምጣት ቀርቶ አባል ሆነው መቀጠል ነበረባቸው? ረጋ ብለው ያስቡ አቶ አያልቅበት!

የፕሮቴስታንት እምነት ያላቸው ሰዎች መሰባሰባቸውን በተመለከተ "የተጠቀሱት ሰዎች ሁሉ የተባለው እምነት ተከታይ ስለመሆናቸው ምን ማረጋገጫ አላቸው?" ሲሉም ጠይቀውኛል። ጥያቄውን ወደ እርስዎ ልመልሰውና፣ እርስዎስ ላለመሆናቸው ምን ማረጋገጫ አለዎት? ከጠቀስኳቸው ሰዎች ውስጥ የሚያውቁት ሰው ካለ "እከሌ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ አደለም" ብለው ይጥቀሱ። ከተሳሳትኩ ለመታረም ዝግጁ ነኝ። ዝም ብለው በጨበጣ የሚከራከሩኝ ከሆነ ጉንጭ ማልፋት ነው የሚሆነው። ለነገሩ ሀቅ ስለተናነቀዎትና በውስጥዎ ጥርጣሬም ስላደረብዎት "ቢሆኑስ ወንጀሉ ምንድነው?" ብለው አረፉ!

በበኩሌ መሰባሰባቸው ክፋት የለውም፡፡ ሆን ተብሎ አንዳንዶቹ እንዲገለሉ ሌሎቹ እንዲሰባሰቡ ማድረግ ግን ከወንጀልም በላይ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ከአራቱ ፓርቲዎች (ስም መጥቀስ አልፈልግም) የአንዱ ፓርቲ አመራር አባላት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የአንድ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፣ የሌላኛው ፓርቲ አመራር አባላት ደግሞ ከግማሽ የማያንሱት የአንድ እምነት ተከታዮች ስብስብ እንደነበር ያሰባሰብኳቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። እንዲህ ያለው መሰባሰብ የሀገሪቱን ፖለቲካ ምን ያህል ሊያውክ እንደሚችል እንኳን አያልቅበትን ለሚያህል "የፖለቲካ ተንታኝ" ጡጦውን ላልጣለ ህፃን የሚሰወር አይመስለኝም።

ባለፈው ጽሁፌ አራተኛ ሴራ አድርጌ ያቀረብኩትን በተመለከተ አቶ አያልቅበት ምንም ዓይነት ያነሱት ነገር ስለሌለ ሃሳቡን እንደተቀበሉት በመቁጠር፣ በጽሁፋቸው መቋጫ አካባቢ ባነሱት አንድ ሃሳብ ላይ አስተያየት ሰጥቼ ጽሁፌን ልቋጭ።

በኢዴፓ ውስጥ የነበረውን የማህተም "ምታ" "አልመታም" አተካሮ በተመለከተ አያልቅበት የማያውቁትን ጉዳይ በማንሳት የተዛባ ሃሳብ አቅርበው አንባቢን ለማሳሳት ሞክረዋል። ባለፈው ጽሁፌ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ከምርጫው በኋላ ቅንጅት አካባቢ የሚታየውም ሆነ የሚሰማው ነገር ጤነኛ ያልመሰለን አንዳንድ የኢዴፓ አባላት፣ (መቼም መቃብራችን ሲቆፈር እያየን እጃችንን አጣጥፈን ዝም ማለት ስላልነበረብን) የአራቱ ፓርቲዎች ውህደት በጥንቃቄ እንዲፈጸም አሰብን። በስንት መከራ ጠቅላላ ጉባዔው ተጠራ፡፡ ጉባዔው መስከረም 11 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ውህደቱን ፈቅዶ ሂደቱ ግን በቅድመ ሁኔታ እንዲፈጸም ወሰነ። አንዱ ቅድመ ሁኔታ "ፓርቲው የሚከስመው ውህደቱ በሁሉም ደረጃ ሲጠናቀቅ" ነው ይላል። ለቅንጅት አመራርነት የተመረጡት 18 ሰዎችም ይህንኑ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት ተሰጣቸው።

አራቱ ፓርቲዎች "የውህደት ስምምነቱን" መስከረም 14 ቀን 1998 በግሎባል ሆቴል ተፈራረሙ። በፊርማውም ስነ ስርዓት ላይ አስፈላጊው ጥንቃቄ ተደረገ። በቅንጅቱ ውስጥ አዲሱ አመራር የስራ አስፈጻሚ ድልድል በወጉ ሳይጠናቀቅ "ሰርተፊኬት መልሱ፣ ማህተም ምቱ" የሚል ነገር መጣ። ኢዴፓን ወክለው በቅንጅት ስራ አስፈጻሚ ውስጥ የነበሩት በበኩላቸው "ይህንን የምናደርገው መዋቅር ተፈጥሮ፣ በሁሉም የቅንጅት መዋቅሮች ውህደቱ ሲፈጸም ነው" የሚል መከራከሪያ ያቀርቡ ጀመር። ነገሩ እየተካረረ መጣ። በሽምግልናም ተሞከረ። አልሆነም። በመጨረሻም ከኢዴፓ የመጣችሁት 18 ሰዎች ተወያይታችሁ ውሳኔችሁን አሳውቁ ተባለ።

ረቡእ ጥቅምት 16 ቀን 1998 ዓ.ም ከዶ/ር አድማሱ በስተቀር አስራ ሰባቱ ሰዎች ተሰብስበው ከቀኑ 9፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት ተወያዩ። በመጨረሻም አስር ለሰባት (10 ፡ 7) በሆነ ድምፅ "በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሰረት ውህደቱ ስላልተጠናቀቀ ማህተም መመታት የለበትም" የሚል ውሳኔ ተላለፈ። ይህም ለቅንጅት በደብዳቤ ተገለጸ። ይሁን እንጂ አቶ አያልቅበት እንዳሉት ሃሳባቸው በብዙሃኑ ድምፅ ውድቅ የተደረገባቸው እነ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ተሰብስበው ሌላ ማህተም አስቀርጸው ወንጀል ውስጥ ገቡ።

አቶ አያልቅበት በዴሞክራሲያዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አምናለሁ የሚሉ ከሆነ ሃሳባቸው የተሸነፈው እነ ዶ/ር ኃይሉ ለብዙሃኑ ውሳኔ ተገዢ መሆን አልነበረባቸውም? ውሳኔው ትክክል ሆነም አልሆነ የብዙሃኑ ሃሳብ መተግበር አልነበረበትም? እርስዎ እንደ ጀግና ያሞገሷቸው እነ ዶ/ር ኃይሉ አሳፋሪ የማፊያ ስራ ነበር የሰሩት፡፡ ደግነቱ እነ ልደቱም ቢሆኑ ቆቅ ስለሆኑ በእለቱ የተያዘውን ቃለ ጉባዔ በሸኚ ደብዳቤ ለምርጫ ቦርድ በመላክ 'እነሱ ለምሳ ሊያደርጓቸው ሲያስቡ ለቁርስ አደረጓቸው።'

አቶ አያልቅበት ስሜታዊ ሳይሆኑ ነገሩን ረጋ ብለው እንዲያስቡት አደራ እላለሁ። የእነ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለብዙሃን ድምፅ አለመገዛት (Tyranny of the Minority) ለዚች አገር የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አንዳችም ፋይዳ የሌለው “የአናርኪስት” አካሄድ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል። ሃሳባቸው የተቸነፈባቸው ሁሉ እየተነሱ ማህተም እያስቀረጹ የብዙሃኑን ድምፅ የሚሽሩ ከሆነ በዚች አገር ዴሞክራሲ የሚባለው ነገር ሊገነባ ቀርቶ ሃሳብ ተለዋውጦ ውሳኔ ማሳለፍ የሚቻልበትም ሁኔታ ሊኖር የሚችል አይመስለኝም።

በመጨረሻም፣ አቶ አያልቅበት የኔ ብእር የዘር ጥላቻና የሃይማኖት ልዩነትን የሚያባብስ መርዝ አይረጭም። በኔ እይታ የጥላቻ ትጥቅ ታጥቀው መርዝ የረጬት እርስዎ ራስዎ ነዎትና የጽሁፍዎን ይዘት እንደገና ሰከን ብለው ቢመረምሩ መልካም ነው እላለሁ፡፡ የኔ ብእር ለሴረኞች መርዝ መሆኑ ግን እርግጥ ነው!